በኮልፌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት

የ6ተኛ ክፍል አማርኛ ሞዴል ፈተና

ጥር 2018 ዓ.ም የጥያቄ

ብዛት፡ 40 የተፈቀደው ሰዓት፡- 1 ሰዓት

## አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የአማርኛ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትዕዛዝ በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጠው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፤ በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው ሰዓት 1 ሰዓት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል። ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

LIVEWORKSHEETS

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም!

**መመሪያ አንድ፡- ከዚህ በታች የቀረቡት ከተራ ቁጥር 1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ ከቀረቡት አማራጮች መካከል በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡**

አንድ የተማረ ሰውና አንድ ያልተማረ ሰው በጀልባ ሲሄዱ ትልቅ አውሎ ነፋስ ተነስቶ ጀልባውን ሊገለብጠው ከወዲያና ከወዲህ እያንገላታ በጣም የሚያስፈራ ሆነ፡፡ አዋቂው ሰውዬ በዚህ ጊዜ እጅግ ፈርቶ ተንቀጠቀጠ፡፡ ያልተማረው ግን ምንም ሳይፈራ ጀልባ እንዳይገለበጥባቸው ከማዕበለ ጋር እየታገለ ከብዙ ጭንቅ በኋላ በደህና ወደ ጠረፍ ወጡ፡፡

ያልተማረው ሰውዬ በጣም እየሳቀ አየው፡፡ "የኛ ሊቅ እኔ ‹ያልተማረ› የተባልኩ ሰው ምንም ሳልፈራ አንተ ግን የተማርክ፣ ብዙ ነገር ታውቃለህ የተባልክ ሰው ይህንን ያህል በፍርሀት ስትንቀጠቀጥ በማየቴ በጣም አድርጎ አሳቀኝ፡፡" እያለ አሾፈበት፡፡

ሰውየው ተናዶ "አንተ ያልፈራህበት ምክንያት ብትኖርም፣ ብትሞትም ለዓለም ምንም የምታጎድል የሌለ መሆኑን ስለምታውቅ ነው፡፡ እኔ ግን ብሞት ለዓለም ብዙ ነገር እንደሚጎድል አውቃለሁና ለዚህ ነው ሞትን በጣም አድርጌ መፍራቴ"አለው፡፡

ምንጭ፡- ከበደ ሚካኤሌ፡ ታሪክና ምሳሌ 1ኛ መፅሐፍ 1948

------1.በምንባቡ ውስጥ "ከማዕበለ ጋር እየታገለ" ሲል ምንን ያመለክታል፡፡

ሀ.ዝናብ መኖሩን ያመለክታል፡፡ ለ.ፀሐይ መኖሩን ያመለክታል፡፡

ሐ.ነፋስ መኖሩን ያመለክታል፡፡ መ.ጎርፍ መኖሩን ያመለክታል፡

LIVEWORKSHEETS

------2.ለዓለም የሚጠቅመው የትኛው ግለሰብ ነው።

ሀ.ሰነፍ ሰው ለ.ደካማው ሰው

ሐ.የተማረው ሰው መ.ያልተማረ ሰው

------3.ምንባቡ የተዋቀረው በስንት አንቀፅ ነው።

ሀ.በአራት ለ.በሶስት ሐ.በሁለት መ.በአምስት

------4.በምንባቡ ውስጥ "ጀልባ" ሲል ምን ማለቱ ነው።

ሀ.በውሃ ላይ የሚጓዝ ለ.በመሬት ላይ የሚጓዝ

ሐ.በአየር ላይ የሚጓዝ መ.በየብስ ላይ የሚጓዝ

------5.በምንባቡ ውስጥ አንቀፅ ሶስት ስንት አይነት ስርዓተ ነጥቦች እናያለን።

ሀ.አንድ ለ.አራት ሐ.ሶስት መ.ሁለት

**መመሪያ ሁለት፡- ከተራ ቁጥር 6-11 ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ በመምረጥ ለመልስ መስጫነት በተዘጋጀው ወረቀት ላይ አስቀምጪ/ጥ/**

------6.ለአንድ ግለሰብ ወይም ነገር የሚሰጥ የግል መጠሪያ ምን ይባላል?

ሀ.የወል ስም ለ.የተጸውዖ ስም ሐ.ተውላጠ ስም መ.የጋራ ስም

-------7.ከሚከተሉት መካከል በትክክል ተነጣጥሎ የተፃፈው ቃል የትኛው ነው?

ሀ.በመንገድ-ኦቻ-ኣችን ለ.በ-መንገድ-ኦች-ኣችን

ሐ.በመንገዶች-ኣችን መ.በመንገድ-ኦች-ኣች-ን

-------8. «ፈሪ ጨነቀው ተርበደበደ፣

ጥይት ዘነበ እሳት ወረደ።

LIVEWORKSHEETS

ውረድ እንውረድ ተባባሉና፣

አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና፡፡»

የሚለው ግጥም ከሚከተሉት የስነ-ቃል ዘርፎች መካከል ለየትኛው ተስማሚ ነው?

ሀ.ሙሾ ለ.እንጉርጉሮ ሐ.ልመና መ.ፉከራ

-------9.ከሚከተሉት ውስጥ በጊዜ አመልካች ተውሳከ ግስ የተፃፈ አረፍተ ነገር የትኛው ነው ?

ሀ.ሩጫውን ያሸነፈው ልምምድ ስላደረገ ነው፡፡

ለ.ለሚቀጥለው ክረምት ለጉብኝት ወደ አዳማ አካባቢ እሄዲለው፡፡

ሐ.መጻህፍት የ እውቀት ምንጭ ናቸው ፡፡

መ.አየለ እራሱን ታሞ ወደ ሃኪም ቤት ሄደ፡፡

--------10.በሃላፊ ጊዜ የተፃፈ አረፍተ ነገር የትኛው ነው ?

ሀ.በእርግጠኝነት ወደ ሰባተኛ ክፍል አልፋለሁ፡፡ ለ.ዛሬ ፈተና እየተፈተንን ነው፡፡

ሐ.ለጉብኝት ወደ ላሊበላ ሄጄ ነበር፡፡ መ.ፈተናው እንዳለቀ ወደ ቤቴ እሄዳለሁ፡፡

--------11.‹‹ሀገራችንን›› በሚለው ውስጥ ስንት ጥገኛ ምዕላዶች አለ?

ሀ.አራት ለ.ስድስት ሐ.ሶስት መ.ሁለት

--------12.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በምዕላድ አከፋፈሉ ስህተት የሚይታይበት የትኛው ነው

ሀ.ቤት-ቸውን ለ.ሜዳ-ዎች -ኡ

ሐ.ገንዘብ-ኤ መ.ውጤት-ኣማ-ነት

--------13.ቤተ መፅሀፍት መጠቀም የሚፈልግ ሰው በመጀመሪያ የመፀሀፉን ርዕስ እና የደራሲውን ስም ይዞ ወደ ቤተ መፅሀፍት አስተናጋጅ ይሄዳል...፡፡ በሚለው ሀሳብ መነሻነት አንቀፅ ለመፃፍ የምንጠቀመው የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልት ------------- ነው?

ሀ.ተራኪ ለ.ገላጭ ሐ.አመዛዛኝ መ.ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

--------14.የእንቀፅ መሰረታዊ አካላት የምንላቸው የትኞቹ ናቸው?

ሀ.ኃይለቃል እና መዘርዝር ለ.ዓ/ ነገር እና ሀረጋት

ሐ.ባለቤት እና ተሳቢ መ.ገላጭ እና ስዕላዊ

-------15.ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ባለ ንብረትን የሚገልፀው ቃል የቱ ነው?

ሀ.መፅሀፍት ለ.መፅሀፎች ሐ.መፅሀፋችን መ.መፀሀፍ

-------16.በአንቀፅን ውስጥ የሚተላለፈውን ሀሳብ ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርብ የአንቀፅ ተዋቃሪ አካል ምን ይባላል?

ሀ.ኃይለ ቃል ለ.መዘርዝር

ሐ.ዋና ዓ/ነገር መ.ሀ እና ሐ መልስ ናቸው።

--------17.በሁለት የተለያዩ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነቶችን የምናሳይበት የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልት ----------- ይባላል።

ሀ.አመዛዛኝ ፅሁፍ ለ.ገላጭ ፅሁፍ

ሐ.ስዕላዊ ፅሁፍ መ.ተራኪ ፅሁፍ

--------18.የተዘረዘሩት አማራጮች መካከል የሚቆጠረው ስም የሆነው የቱ ነው?

ሀ.እውቀት ለ.ተማሪ ሐ.ጨለማ መ.ብርሀን

--------19."የኢትዮጲያ መድን ድርጅት" በአፅዕሮተ ቃል አጥሮ ሲፃፍ ትክክለኛ መልስ የያዘው አማራጭ የቱ ነው?

ሀ.የ.ኢ.መ.ድ ለ.የ.መ.ድ ሐ.ኢ.መ.ድ መ.ኢት.መድ.ጅር

LIVEWORKSHEETS

---------20."ፍየል" የሚለው ቃል ፉካሬያዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

ሀ.ቅጠል በሊታ እንስሳ ለ.ለፍላፊ

ሐ.ዝመተኛ መ.ረባሽ

---------21."ተማሪዎቹ ወደ ትምህርት ቤት ሄዱ።" በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የወል ስም የትኛው ነው?

ሀ.ተማሪዎች ለ.ሄዱ ሐ.ወደ መ.እነርሱ

______22.ከዚህ ቀጥለው ተዘበራርቀው የቀረቡ ዓ.ነገሮች ተስተካክለው ሲፃፉ፡-

1.ትምህርት ቤት የሰልፍ ስነ-ስርዓት አልቆ ደረስኩኝ።

2.ከእቅልፌ አርፍጄ ተነሳሁ።

3.ቁርሴን ሳልበላ ተጣድፌ ከቤት ወጣሁ።

4.ርዕሰ መምህሩ አንበረከከኝ።

5.ማታ ፊልም ሳይ አምሽቼ ተኛሁ።

ሀ.1,2,3,4,5 ለ.5,3,2,4,1 ሐ.5,2,3,1,4 መ.1,4,2,5,3

_______23.ወንፊት ለሆኑ ሰዎች ሚስጥር ማጋራት አያስፈልግም። የተሰመረበት ቃል

አውዳዊ ፍቺ ______ነው።

ሀ.ተጫዎች ለ.ዱቄት መንፊያ ሐ.ሚስጢር ጠባቂ መ.ወሬኛ

_______24.የህፃኑ ልጅ ለቅሶ የእናቱን አንጀት በላ። የተሰበረበተ ቃል አውዳዊ ፍቺ_____ነው።

ሀ.ተመገበ ለ.አሳዘነ ሐ.አሸነፈ መ.ሰረቀ

_______25. በከተማ ውስጥ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ። የተሰመረበት ቃል _______ነው።

LIVEWORKSHEETS

ሀ.ረቂቅ ስም ለ.የተፀውኦ ስም

ሐ.የወል ስም መ.የነገር ስም

______26.ቀጥሎ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ነፃ ምእላድ የሆነው የቱ ነው

ሀ.መፅሀፌ ለ.ሀገራችን ሐ.ትምህርት መ.ተራራማ

______27. አንድን ሁነት በጊዜ ቅደም ተከተል የሚያቀርብልን የድርሰት አፃፃፍ አይነት____ነው።

ሀ.አመዛዛኝ ድርሰት ለ.ተራኪ ድርሰት

ሐ.አወዳዳሪ ድርሰት መ.ገላጭ ድርሰት

______28.የሃገራችንን የሚለው ቃል በምዕላድ ተከፋፍሎ ሲፃፍ የቱን ይመስላል?

ሀ.የሀገር-ቻችን-ን ለ.የ-ሀገር -ኣችን -ን

ሐ.ሀገር-ኣችን -ን መ.የ-ሀገር -ኣ-ችንን

----------29."ንብ" የሚለው ቃል እማሬያዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

ሀ.ትጉህ ለ.ታታሪ

ሐ.ሰራተኛ መ.ማር አምራች በራሪ ፍጡር

--------30.ስለ አስተዋፅኦ ወይም ቢጋር መንደፍ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ.የሃሳብ ድግግሞሽን ለማስቀረት ለ.የሃሳብ ፍሰትን ለመጠበቅ

ሐ.የሃሳብ ድግግሞሽ እንኖር ማድረግ መ.የይዘት ቅደም ተከተልን ለመጠበቅ

LIVEWORKSHEETS

---------31.ልጁ ፈተና እየተፈተነ ነው። የተሰመረበት ግስ የሚገልፀው የምን ጊዜ አይነትን ነው?

ሀ.የትንቢት ጊዜ　　ለ.የኃላፊ ጊዜ

ሐ.የወደፊት ጊዜ　　መ.የአሁን ጊዜ

---------32.ከሚከተለት ውስጥ ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ፆታን የሚገልፀው ተውላጠ ስም የቱ ነው?

**መመሪያ ሶስት፦ ከተራ ቁጥር 33 እስከ 36 ድረስ ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ የሚሆናቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የሚሆናቸውን ፊደል ምረጥ/ምረጪ።**

---------33.ምስጢር

ሀ.ድብቅ　　ለ.ውሸት　　ሐ.እውነት　　መ.ገሃድ

---------34.በጋራ

ሀ.በህብረት　　ለ.በአንድነት　　ሐ.በግል　　መ.ብዙ

---------35.ባህላዊ

ሀ.ዘመናዊ　　ለ.ታሪክ　　ሐ.የሚያምር　　መ.ጥንታዊ

---------36. ማግኘት

ሀ.ማፍራት　　ለ.ማጎልበት　　ሐ.ማጣት　　መ.መኖር

LIVEWORKSHEETS

መመሪያ ሶስት፦ ከተራ ቁጥር 37 እስከ 40 ድረስ ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆናቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የሚሆናቸውን ፊደል ምረጥ/ምረጪ።

------- 37.አፀፋ

ሀ.ውሸት ለ. መንገድ ሐ. ምላሽ መ.ንዴት

--------38.መቅሰም

ሀ.መማር ለ. ለመውጣት ሐ. ማየት መ.መታው

--------39.አመል

ሀ.ፀባይ ለ. ክፉ ሐ. ባህሪ መ.ሀናሐ መልስ ናቸው

--------40.ሀሴት

ሀ.ሀዘን ለ. ደስታ ሐ. ለቅሶ መ.ንዴት

LIVEWORKSHEETS